# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

29



ሰፊው ሕዝብ የሕዝባዊው ሠራዊት አስተማማኝ ደጀን ነው

ሰኔ ፴ — ፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

# ርእሰ አንቀጽ

# ሕዝባዊ ሠራዊት ለነቃ ፣ ለተደራጀ ፣ ለታጠቀ ሕዝብ ትግል

የኢትዮጵያ አብዮት ዓላማ ፊውዳሊዝምን ፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ደምስሶ በነሱ መቃብር ላይ የሰፊው ሕዝብ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለአንዳች ገደብ የሚከበሩበት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም ነው ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደዚህ ወሳኝ ወደሆነው ድል የሚጓዘው እንዴት ነው ? ለዚህም መልሱ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ በሚገባ ተገልጿል ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የሚገነባው ነቅቶ ፣ ተደራጅቶና ታጥቆ በጠላቶቹ ላይ በሚያካሂደው አመጽ አማካይነት ነው ። ተደጋግሞ እንደተገለጸው ይህንን ትግል በሚገባ ከግቡ ለማድረስ የወዝአደሩ ፓርቲ ፣ በሱ የሚመራ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት ፍቱን የሆኑና ሌላ ምንም ዓይነት አማራጭ የሌላቸው የትግል መሣሪያዎች ናቸው ።

እንግዲህ ጥያቄው ዛሬ አብዮታችን የት ደርሶልእጅግ ደግቅ በሆነ ሁኔታ ባለፈው ቅዳሜ ሰኔ ፲፰ ቀን ፸፱ ዓ.ም. የተመረቀው ሕዝባዊ ሠራዊት በዚህ ትግል ውስጥ ምን ቦታ ይኖረዋል የሚል ነው።

ዛሬ አብዮታችን በደረሰበት ሁኔታ ብዙ ችግሮች ቀስፈው እንደያዙት እናያለን ። የሀገራችንና የአብዮታችን ከውጭ መከበብና ከውስጥ እየተቦረቦረ መሔድ ይፋ እየሆነ ሔድዋል ። የእናት ሀገራችን አንድነትና ሕልውና በሰሜንና በደቡብ ምሥራቅ ተደፍሯል ። በሱዳንና በሱማሊያ የሚሠለጥኑና የነሱ ድጋፍ ያላቸው ፀረ አብዮት ኃይሎች አገራችንን በመውረርና አብዮታችንን በመውጋት ላይ ናቸው ። መሳፍንቱ ፣ ልጆቻቸውና አድኃሪዎቹ የኤርትራ ግንባሮች በውጭ ኃይሎች እየተረዱ በአብዮታችንና በአንድነታችን ላይ በማመጽ አልተቆጠቡም ። አድኃሪውን ቢሮክራሲ እጅግ በረቀቀ ዘዴ ውስጥ ውስጡን በማደራጀትና በሱ አማካኝነት በአብዮቱ ሠፈር ሰርገው በመግባት አብዮታችንን በስተጀርባ በመውጋት ላይ ናቸው ። ከዚህ ከበባና ቡርቦራ ለአብዮታችን የሚፈልቁት ችግሮች እጅግ ብዙና የተወሳሰቡ ናቸው ። ኢኮኖሚው እንዲናጋ ፣ ምርት እንዲቀንስ ፣ የማከፋፈያው ሰንሰለት እንዲበጠስ ፣ ሰፊው ሕዝብ ከየአቅጣጫው የሚቃጣበት ጦርነትና ሊያስከትል የሚችለው እልቂትና ሙከራ . . . ተስፋ አስቆርጦትና አስመርሮት በገዛ አብዮቱ ላይ እንዲያምፅ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ። ሱማሌ የባቡሩን ሐዲድ መምታቷ ፣ ሱዳን በኢትዮጵያ የተመዘገቡ አውሮፕላኖች በግዛቷ ላይ እንዳይበሩ ማገዷ ፣ አድኃሪው ቢሮክራሲ ፣ በማበብ ላይ ያሉትን ሕዝባዊ ድርጅቶች ለማፈንና ተስፋ ለማስቀረጥ የሚያደርገው አሻጥር ፣ አድኃሪዎች በአብዮቱ ሠፈር ለመንዛት የሚሞክሩት ነጭ ሽብር . . . ወዘተ ይኸ ሁሉ የተቀነባበረ ፀረ አብዮት ሴራ አንዱ አካል መሆኑ ነው ። ጥረቱ ሁሉ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በነዚህ ችግሮች ተውጦና ሐሳቡ ሁሉ በነሱ ተይዞ ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያችንን የመገንባቱን ነገር ችላ እንዲል ለማድረግ ነው ። ጥረቱ ሁሉ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን ሁሉ ችግሮች ከአብዮቱ ችግሮች ነጥሎ እንዲመለከት ፣ ጨርሶ ሊሳካ በማይቻል ቅዠት ከአብዮቱ ግብ መምታት በመለስ እነዚህን ችግሮች በተናጥል እፈታለሁ ብሎ ከንቱ መፍጨርጨር እንዲያደርግና ወድቆ እንዲሰባበር ነው ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮታውያን ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግመው ደጋግመው የሚያስተምሩት ሐቅ አለ ። የመጣ ችግር ቢመጣ መፍትሔው ከአብዮቱ ትግል መግፋት ውጭ አይገኝም ። እነዚህ ችግሮች የሚወገዱት አብዮቱ ድል ሲመታ ብቻ ነው ። ለዚህም ሰፊው ሕዝብ ከሁሉም በፊት በራሱ ኃይል ተማምኖ ነቅቶ ተደራጅቶና ታጥቆ የነዚህን ችግሮች ምንጭ የሆኑትን ፀረ አብዮት ኃይሎች ማለትም ፊውዳሊዝምን ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን መደምሰስ ይኖርበታል ። ይህ ቀላልና ግልጽ ዕውነት ይመስላል ። ነገር ግን በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ከአሻጥረኛው የውስጥ አርበኛ አንስቶ እስከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ድረስ ያለው የፀረ ሕዝብ መንጋ የሚሞክረው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን ሁሉ ችግሮች ከአብዮቱ መግፋት ውጭ እንዲመለከታቸውና መፍትሔያቸውንም ከሕዝቡ መንቃት መደራጀትና መታጠቅ ውጭ ሊገኙ እንደሚችሉ አስመስሎ ለማቅረብ ነው ። እንደዚህም ስለሆነ አድኃሪው ቢሮክራሲ «የነቃ ፣ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ትግል ያሸንፋል» ሲባል ማሾፍ ጀምሯል ። ሰፊው ሕዝብ ለመንቃት ለመደራጀት ለመታጠቅ የሚያደርገው ትግል ያፋፍም ሲባል ለዚህም ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ ይታወቁለት ሲባል «ጦርነት ላይ እያለን እንዴት ዲሞክራሲ ይባላል» በማለት ያስተጋባል ። ከዚህም አልፎ የሰፊውን ሕዝብ መንቃትና መደራጀት በማፈን የካቲት የወለዳቸውን ሕዝባዊ ድርጅቶች ለማሸበር ፣ ቅስማቸውን ለመስበር ለመበተንና በዚህም የሕዝቡን ትግል ለማዝረክረክ ይሞክራል ። አብዮታውያን ግን ዛሬ ሀገራችንን ያጋጠሟት ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት በሰፊው ሕዝብ የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ተሳትፎ ብቻ እንደሆነ ያምናሉ ። ስለሆነም ለነቃ ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ ሕዝባዊ ትግል ይሟገታሉ ። ይህንን የነቃ ተሳትፎ ለማስገኘትም «ጦርነት ላይ ስላለን ፣ በጠላት ስለተከበብን ዲሞክራሲ አያስፈልግም» የሚለውን አስቂኝ ክርክር አሽቀንጥረው በመጣል እንዲያውም «ከጦርነቱ በድል አድራጊነት ለመውጣት ፣ የጠላትን ከበባ ለመበጣጠስ የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ማለትም ዲሞክራሲ ያስፈልጋል» ይላሉ ። ለዚህም ይታገላሉ ።

በዚህ አንጻር ባለፈው ሰሞን በታላቅ ግርማ ሰልፉን ያሳየውን ሕዝባዊ ሠራዊት ከሁለት አቅጣጫ መመልከት ይቻላል ። የሀገራችን ችግሮች ሁሉ ከአብዮቱ ተነጥለው እንዲታዩለት የሚሻው አድኃሪ አመለካከት ይህንንም ሕዝባዊ ሠራዊትና የሚያካሔደውን ትግል በሚሊዮን ከሚቆጠረው የሰፊው ኢትዮጵያ ሕዝብ አመጽና ትግል ገንጥሎ ለመመልከት ይፈልጋል ። እንዲያውም ከዚህ አልፎ ተርፎ በዚህ ሕዝባዊ ሠራዊት መፈጠር የተነሳ ለዚያ ፣ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ የተነደፈው «የወዝአደር ፓርቲ ፣ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት» ለሚለው ፍቱን ጉዳና ሌላ አቋራጭ የተገኘለት አስመስሎ ቁጭ ይላል ። ይህ የዓለምን ተመልካቾች ያስደነቀና ይህ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያኮራ ሕዝባዊ ሠራዊት «ወሳኝ» የሆነውን ትግል ሊያካሂድ የሚችል አስመስሎ ያቀርበዋል ። አብዮታውያንስ? አብዮ

ታውያን ይህንን ሕዝባዊ ሠራዊት ከላይ የተጠቀሰውን ሳይንሳዊ የትግል ጐዳና እንደሚያስትና እሱን እንደሚያስለቅቅ አቋራጭ አድርገው አይመለከቱትም ። ለአብዮታውያን በሚሊዮን የሚቆጠረውን ሰፊ ሕዝብ ተክቶ አብዮቱን ከግብ ሊያደርስ የሚችል ምንም ዓይነት ኃይል የለምና ። ስለሆነም ሕዝባዊውን ሠራዊት አብዮትን ባቋራጭ እንደማድረጊያ ኃይል አይቆጥሩትም ። ፍቱንና ሳይንሳዊ ለሆነው በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ለተጠቀሰው የትግል ሂደት ምትክ አድርገው አይቆጥሩትም ። ዛሬ የኢትዮጵያን አብዮት ከግቡ ለማድረስ ማርክሲስት ሌኒንስቶች ሕብረታቸውን መስርተው የወዝአደሩን ፓርቲ ለመመስረት ፤ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርንና ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊትን ለመገንባት እየታገሉ ናቸው ። የትግሉ ፍቱን መንገድ ይኸው ብቻ ነውና ።

ስለሆነም ሕዝባዊው ሠራዊት በዘመተበት ሁሉ በተለይም ደግሞ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ዓላማው ሀገራችንን ወጥረው ይዘው አብዮታችንን ለመቀልበስ የሚፍጨረጨሩትን ኃይሎች ተቋቁሞ ሰፊው ሕዝብ አሁን ካለበት በይበልጥ እንዲነቃ ፤ በይበልጥ እንዲደራጅ ፤ በይበልጥ እንዲታጠቅ ለማድረግና ወሳኙን ትግል አካሂዶ ድል ለማድረግ እንዳበቃ የሚያስፈልገውን ፋታ ለመስጠት ነው ። ከየካቲት ፷፮ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በንቃት በድርጅትና በትጥቅ ገፍቶ እዚህ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው ፤ እንዲያውም ይህንን ያህል የነቃና የተደራጀ ሕዝባዊ ሠራዊት ለማሰለፍ የቻለው የኢትዮጵያ ወዝአደሮች ፤ አርሶ አደሮች ፤ አብዮታዊ መለዮ ለባሾችና ሌሎችም አብዮታውያን በደማቸው እየቀዘቀዙ ከፀረ አብዮት ኃይሎች ተከላክለው ለጭቁኑ ሕዝብ የመንቂያና የመደራጃ ፋታ በማስገኘታቸው ነው ። ከመደበኛው ሠራዊት ጐን የሚሰለፈው ሕዝባዊ ሠራዊትም በዚህ ቆራጥነትና በዚህ አብዮታዊ ወኔ በመነሳቱ የሰፊውን ሕዝብ የመንቃት የመደራጀትና የመታጠቅ ተጋድሎ የሚያፋፍም ኃይል እንዲሆን የአብዮታውያን ሁሉ ምኞት ነው ።

እንግዲህ አብዮታውያን ነገሩን የሚመለከቱት በዚህ መልክ ነው ። እናት አገራችን ኢትዮጵያ የአንድነቷንና የአብዮቷን ጠላቶች በሙሉ ለመደምሰስ የምትችለው በነቃ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝቧ ትግል ነው ። ለዚህ ዓይነት ረዥምና የተወሳሰበ ትግል ምንም ዓይነት አማራጭ ምንም ዓይነት አቋራጭ የለም ። ዛሬ ሰፊው ሕዝብ እንዳይነቃና እንዳይደራጅ ከያለበት ፀረ—አብዮት ኃይሎች ሲያዋክቡት ይታያሉ ። ሕዝባዊው ሠራዊት እነዚህን ፀረ አብዮትና ፀረ አንድነት ኃይሎች ተቋቁሞ ሰፊው ሕዝብ ለመንቃት ፤ ለመደራጀትና ለመታጠቅ በዚህም እነዚህን ጠላቶቹን ለመደምሰስ የሚያስፈልገውን ፋታ ያስገኝለታል ። ግን ፋታ ማግኘቱ ብቻ አይበቃም ። መደበኛው መለዮ ለባሽና ሕዝባዊው ሠራዊት በደሙ እየዋዠቀ በሚያስገኝለት ፋታ ሰፊው ሕዝብ ሌት ተቀን ሳይል ባፋጣኝ መንቃትና መደራጀት አለበት ። ሰፊው ሕዝብ በፍጥነት እንዲነቃ ፤ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ደግሞ የንቃት ፤ የድርጅትና የትጥቅ አስተማማኝ መሣሪያ የሆኑት የዲሞክራሲ መብቶች ያለገደብ ሊለቀቁለት ይገባል ፤ ከዚህ ሌላ የአብዮታዊ ድል ዋስትና ምንም ሊኖር አይችልም ።

የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ትግል ያሸንፋል !!
ድል የሰፊው ሕዝብ ነው !!